# የሱዳኖችን የጦርነት ቋንቋ ማን እየሰማ ነው?

*በነብዩ ተድላ*

የደቡብ ሱዳን ህዝብ ለዓመታት ከዘለቀው የሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት ተላቆ 98 በመቶ የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ ከካርቱም አገዛዝ የሚያፋታውን ነፃነት ማግኘትን ፈቅዶ ከሰሜን ሱዳን ለመገንጠል በሪፈረንደሙ የዜግነት መብት እናገኝ በማለት ምርጫውን ማሳወቁ ይታወሳል፡፡ በዚህም እ.ኤ.አ. በሐምሌ 09/2012 ደቡብ ሱዳን የዓለማችን አዲሲቷ አገር በመሆን የዓለም መንግሥታትን ተርታ ተቀላቅላለች፡፡

ይህ የደቡብ ሱዳን ነፃነት ሳይታወጅ ገና አስቀድሞ ለሁለቱ ሱዳኖች የራስ ምታት የሆኑና ለመንግስታቱ በቀላሉ የማይፈቱ የቤት ሥራዎች በደቡባዊ ኮርዶፋንና በብሉ ናይል ግዛቶች መፈጠር የጀመሩት ሁከቶች ሁለቱ ሱዳኖች አብረው የሚዘልቁ እንደማይሆኑ ቀዳሚ አመላካቾች ነበሩ፡፡ ከዚሁ ጋር የሁለቱ ሱዳኖች ድንበር በቅጡ አለመከለል፣ ከነፃነት በኋላ የደቡብ ዜጎችም ሆኑ የሰሜኑ አንዱ በሌላው ምን አይነት ደረጃ ይኖራቸዋል፣ አቢዬና ሄግሊግ የተሰኙትና በነዳጅ ሀብታቸው የበለፀጉና ሁለቱ ሱዳኖች የሚሻኮቱባቸው አካባቢዎችን ጨምሮ ሌሎች አወዛጋቢ ቦታዎች ለሰሜኑ ይሁን ለደቡቡ የመጨረሻ ወሳኔ አለመኖሩ ለሱዳኖች ራስ ምታት መቀጠል እንደምክንያት ይጠቅሳሉ፡፡ በተጨማሪም ሱዳን እንደአገር አንድ በነበረችበት ወቅት ከዓለምአቀፍ አበዳሪ ተቋማትና ሀገራት ያለባትን ብሔራዊ ዕዳ የአከፋፈል ሁኔታ፣ የነዳጅ ገቢ ክፍፍልና ደቡብ ሱዳን ነዳጅ በሰሜN ሱዳን በኩል ወደ ሱዳን ወደብ ለማስተላለፍ በምትከፍለው የትራንዚት ክፍያ ላይ አለመስማማት ሁለቱ ሱዳኖች በሠላም ተጎራብተው እንዳይዘልቁ ሰቅዘው የያዙ ችግሮች ነበሩ፡፡ ናቸው፡፡

ከነዚህ የቅድሚያ ችግሮች ይልቅ ግን የሁለቱ ሱዳኖች ጥል ምክንያቶች ከ50 ዓመታት በላይ የሚዘልቅና የሱዳን የወቅቱ ቅኝ ገዥ እንግሊዝ ሱዳንን እ.ኤ.አ. በ1956 ለቃ ስትወጣ የሚጀምሩ ይሆናሉ፡፡ አገራቱ ከሚዋሰኑበት የ2,100 ኪ.ሜ. በላይ የጋራ ድንበር ውስጥ በ1,800 ኪ.ሜ. ያህል በሚሆነው ድንበር ላይ መስማማት ላይ አልደረሱም፡፡ ሰሜን ሱዳን ቅኝ ገዥዋ እንግሊዝ ስትወጣ ያሰመረችውን ድንበር ማጽናት ሲፈልጉ ደቡቦቹ አዲስና በድርድር ላይ የተመሠረተ ድንበርን መተግበር ይፈልጋሉ፡፡ ከድንበሩ በላይም በቅርቡ የደቡብ ሱዳን ጦር እ.ኤ.አ. በኤፕሪል 10 የወረራትን የደቡብ ኮርዶፋን ግዛት አካል የሆነችው ሄግሊግን ጨምሮ ሌሎች በሰሜኑ የሚዋሰኑ ቦታዎችን ይግባኝ ማለት ይዟል፡፡

ይህ ደግሞ የሱዳንን ለሁለት መከፈል በአመቻቸውና የደቡብ ሱዳንን እንደ ሀገር መፈጠር በአረጋገጠው የ2005 አጠቃላይ የሠላም ስምምነት (Comprehensives Peace Agreement) ላይ ለሰሜኑ እንዲሆኑ የተወሰኑ ቦታዎችን ጨምሮ እንደሆነ መገንዘብ ያሻል፡፡

የሰሜኑ አረቦችና እስላሞች ከደቡቦቹ ክርስቲያን አፍሪካውያን ጋር ለዓመታት በዘለቀው ጦርነታቸው ከ2 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ህይወቱን ገብሮበታል፡፡ በርካቶች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ የካርቱም አስተዳዳሪዎች ደቡቦቹን ለዘመናት ከሱዳን የልማትና የዕድገት እንዲሁም ሌሎች ሰብአዊና ማህበራዊ ግልጋሎቶችና ትሩፋቶች አግልለው ማቆየታቸው የችግሩ መሠረታዊ ምንጭ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ደቡቦቹ በቀድሞው ዶ/ር ጆን ጋራንግ መሪነት የነፃነት ትግላቸውን ሲጀምሩ የቀድሞው የትግል መዳረሻ የራሷን ነፃነት በራስ ወስና ከሱዳን የተፋታች ደቡብ ሱዳንን መፍጠር ሳይሆን በአንድ አገር ማዕቀፍ ስር ነፃነቶችና መብቶች የተከበሩበት የራስ ገዝ አስተዳደርን በጁባ መመስረት ነበር፡፡ እ.ኤ.አ. ከ1983–2005 የተደረገውን የእርስ በርስ ጦርነት ተከትሎ የተፈረመው አጠቃላይ የሠላም ስምምነት እስኪፈረም ድረስ፡፡

<u>ሄግሊግን ማጥቃት ለምን\</u>

በቅርቡ የደቡብ ሱዳን ወታደሮች ሄግሊግን ሲወሩ አብዛኛው የዓለምአቀፍ ማህበረሰብ ከደቡብ ሱዳን ተጨባጭ የኢኮኖሚ አቅም አንፃር መጥኖ መደቆስ የማይችል ቦክስ ለምን ይሰነዝራል? ለምንስ ፀብ አጫሪ ይሆናል? በሚል በደቡብ አስተዳዳሪዎች ላይ የተመድ ዋና ፀሐፊን ጨምሮ በርካታ ባለሥልጣናትና ተንታኞች እንዲሁም የሚዲያ ተቋማት ወቀሳቸውን በሂስ መልክ ሲያቀርቡ ቆይተዋል፡፡ በእርግጥ የሰሜን ሱዳን ኃይሎች አስቀድመው የአበ!ዬን ግዛት ማጥቃታቸውና በደቡብ ኮርዶፋንና የብሉ ናይል ግዛቶች የሚገኙ የSPLA North ኃይሎችን ለማጥቃት ሲሉ በቦንብ ለተከታታይ ግዜያት መደብደባቸው እንዲሁም በዳርፉር ያለው ችግር ለአሁኑ የሄግሊግ ግጭት ድምር ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገለፃል፡፡ በዚህ መነሻም የካርቱም መንግስት ቀዳሚ ወራሪ እንደሆነ ክርስቶፈር አሌሲ የተሰኙ የአሜሪካ የውጭ ግንኙነት ም/ቤት ተመራማሪ ይገልጻሉ፡፡ እንደሳቸው አባባል በዚሁ ትንታኔ መሠረት ጥፋተኛው ደቡብ ሳይሆን የሰሜኑ መንግስት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሌሎች የፖለቲካ ተንታኞች በበኩላቸው ደቡብ ሱዳን በሰሜኑ የሱዳን ግዛት ከሚንቀሳቀሱ የተለያዩ አማፂ ኃይሎችና ሌሎች የሱዳን መንግስት ከሥልጣን

እንዲወገድ ከሚሹ ኃይሎች ባገኘው አይዞህ መባል በተሰማው የልብ ልብ ሄግሊግን እንዳጠቃና የካርቱም መንግስትን ከሥልጣን ለማውረድ ያለመ የተሳሳተ ዓላማ በማራመድ ላይ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ደቡብ ሱዳኖች ሄግሊግን ሲወሩ በምን ሂሳብ እንደሆነ ለብዙዎች አጠያያቂ ሆኗል፡፡ ራምዚ ባሮውድ የተሰኙ የፖለቲካ ተንታኝ ወረራውን በቀጣይ ከሰሜኑ ጋር በሚደረጉ ድርድሮች ጠንካራና የበላይ መስሎ የገዘፈ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ስብዕና ይዞ ለመቅረብና በጠረጴዛ ዙሪያ ተደማጭነታቸውን ከፍ ለማድረግ የታሰበ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

በሌሎች ደግሞ ይህ የደቡቡ ሱዳን ያልተጠበቀ ወታደራዊ እንቅስቃሴ የካርቱም መንግስት በአሁኑ ወቅት ምሳር የበዛበት የወደቀ እንጨት ነው ብሎ በማሰብ በሰሜን ከሚንቀሳቀሱ የዳርፉር፣ የደቡብ ኮርዶፋንና የብሉ ናይል ከመሰሉ አማፂ ኃይሎች ጋር በጋራ በመተባበርና ሌሎች የአልበሽር መንግስት እንዲወገድ ከሚሹ አካላት ጋር አንድ ላይ ቢሠሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ የታሰበ ስሌት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በተለይ አንዳንድ ምዕራባውያን የሰሜኑን መንግስት እጅ ለመጠምዘዝ ካልሆነም ለማውረድ ካላቸው ፍላጎት ጋር ተያይዞ የፖለቲካና የሎጀስቲክስ ድጋፍ ለደቡቡ ሊያደርጉ ይችላሉ የሚል ሀሳብ የሚሰጡ ተንታኞችም አሉ፡፡ ጥያቄው በእርግጥ የደቡቡ ኃይል ሄግሊግን ጥሎ ከመውጣቱ በፊት ይህ መሠል ድጋፍ ወይም ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ እገዛ ተሰጥቶት ነበር ወይ ነው፡፡

የደቡብ ሱዳን ወታደራዊ ኃይል የሄግሊግ ነዳጅ ማምረቻ ለምንና በምን የፖለቲካና ወታደራዊ ሂሳብ ለማጥቃት ፈለገ ሲባል በእርገጥ ምላሹ ጥቃቱን የፈፀመው አካል ብቻ የሚመልሰው ቢሆንም መላምቶችን መሰንዘር ይቻላል።

ጁባ ከካርቱም ጋር ያለውን አለመስማማት እስኪፈታ ድረስ ነዳጅ ማምረቱን ያቆመ ቢሆንም ሰሜን ሱዳን በሄግሊግ አማካኝነት የነዳጅ ምርቱን ቀጥሎ ቆይቷል። ይህ ምርት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ይውል የነበረ ሲሆን የሄግሊግ ጥቃት የአብረን እንሙት የዜሮ ድምር ሂሳብ ሊሆን ይችላል።

**ሌላው ግምት የካርቱምን መንግስት ለመጣል በአገሪቱ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ሌሎች የታጠቁ ኃይሎች ጋር በጋራ በመሆን ጥቃት ለመፈፀም ማቀድና በተለይም ይህን ዓላማ ለማሳካት የሰሜኑን የኢኮኖሚ ጥንካሬ ማዳከምና ሽባ ማድረግ ይህንንም ተከትሎ የአረቡን ዓለም የህዝብ አመፅ የመፍጠርና የመንግስትን ስር የመገዝገዝ ሥራ የመስራት ዕቅድ እንደሆነም ማሰብ ይቻላል፡፡**

**ከዚህ ባሻገር ከዚህ ቀደም የሰሜን ሱዳን ኃይል በአቢዬ ላይ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን በተለይም በዲንቃ-ኖክ ተወላጆች ላይ ጥቃቶችን በመሰንዘር ስፍራው የሰሜን ዝርያ ያላቸው የሚሲርያ ጎሣ አባሎች ብቸኛ ክልል እንደሆነ ሲያውጅ ቆይቷል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ በጥቂት ቀናት ውስጥ ለቆ የወጣ ቢሆንም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የደቡብ ኃይል የመደራደሪያ ክንዱን ለማፈርጠም የወሰደው ስትራቴጂያዊ እርምጃ ሊሆንም ይችላል፡፡ ሆኖም በእርግጥ ደቡቦቹ እንዳሰቡት ወታደራዊና ዓለምአቀፍ የዲፕሎማውሲ ጫና በካርቱም ላይ ፈጥረዋል? ምላሽ ይሻል፡፡**

የካርቱምና ጁባ አስተዳዳሪዎች ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን ለማስፈፀም ሁልጊዜ የሚጨረሻ **ጥግ** አማራጮችን እስከ ወታደራዊ ግጭት መውሰድ (Brinkmanship) የለመዱ በመሆኑ አሁን የተከሰተው ግጭት በዚሁ እንደሚቀጥል ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የደቡብ ሱ**ዳ**ን ነፃ አወጪ ኃይል ሄግሊግ**ን** በወረረ ከሁለት ሣምንት ባልዘለለ ጊዜ ለቆ የወጣ ቢሆንም ደቡብና ሰሜኑ ከሄግሊግ ባሻገር በደቡብ ኮርዶፋን፣ ብሉ ናይልና ሌሎች የድንበር ግዛቶች ቀጥተኛ ያልሆነው ወታደራዊ ፍጥጫቸው (Proxy War) መቀጠሉ አይቀርም፡፡ ደቡብ ሱዳን የዳርፉር አማፅያን እንደምትረዳ የሚቀርቡ አሉባልታ**ና ክሶችም እንዲሁ፡፡**

## <u>የ**ሱዳኖቹ** ተግዳሮቶች</u>

ደቡብ ሱዳን ነፃነቷን ከማወጇ **በፊት የነበረውና** ካወጀችም በኋላ በአገሪቱ እግር ከወርች ጠፍንጎ የሚይዘው ድህነት መቀጠሉ አልቀረም፡፡ ማይምነት በተለይም ከደቡብ ሱዳን ሴቶች 90 በመቶው ባልተሟሉበት፣ አነስተኛ የጤና ጥበቃ ሽፋን በሚገኝበት፣ የመሠረተ ልማት አለማስፋፋትና የደቡብ ሱዳን ወታደሮችና በየደረጃው ያሉ አስተዳዳሪዎች መሠረታዊ የሆኑ የሠብዓዊ መብት ጥሰቶች **ያደርሳሉ ተብሎ ክስ በሚቀርብባት** ደቡብ ሱ**ዳን** የነፃነት ማግስት አልጋ በአልጋ እንዲሆን አላስቻለም፡፡

**በ**ደቡ**ብ** ሱዳን ችግሮች **እ**ንደ ክዋክብት በበዛበት አገር መንግስት **ችግሮችን ከመፍታት አንፃር** ከየት ሥራውን በቅጡ እንኳን እንደጀመረ ለማወቅ ያዳግታል፡፡ ደቡብ ሱዳን ዛሬ የአፍሪካ አዲሲቷ የነዳጅ አምራች

ከሆነች በኋላም የጁባ አስተዳደር ይህን የአገሪቱን አዲስ የገቢ ዘርፍ የማስተዳደር ብሉም የአገራቱን ኢኮኖሚ ከነዳጅ ባለፈ በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ እንዲተማመን ለማድረግ የመንግስቱ ጠንካራ የልማት ፖሊሲ ቀረፃና አፈፃፀም አቅምን ማንባት ይፈልጋል፡፡ **የጦርነት ችግር፣ደካማ የፖለቲካ ስነምህዳር፣ ህገወጥ የመሳርያ ዝውውር፣ የፖሊሲ ትንተና እና ስትራቴጂክ ፖሊሲ የመንደፍ አቅም ደካማ መሆን እንዲሁም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል አለመኖር ታላቅ የሀገሪቱ ፈተናዎች ናቸው፡፡** የአገሪቱ የልማት ባለሞያዎች ጭምር እንደሚስማማበት የደቡብ ሱዳን መንግስት መሠረታዊ አገልግሎቶችን በብቃት የሚሰጥና ሰብአዊ መብቶች በቅጡ የሚከበርባት አገር ለመፍጠር የአንድ ትወልድ ጊዜ እንደሚፈልግ ይገለፃል፡፡

በደቡብ ሱዳን ከነፃነት በኋላ በግልጽ የተከሰቱና በፊትም እንደነበሩ የሚነገረው የጎሣ ልዩነትን በሰለጠነ መንገድ ያለማስተናገድ **ችግር** በቅርቡ በጀንግሌ ግዛት የሉዋኑዌርና የሙርሌ ጎሣዎች ግጭት አፉን ከፍቶ በግልፅ መውጣቱ የጁባ መንግስት በጉዳዩ ዙሪያ ብዙ ሥራዎች እንደሚጠብቁት ያሳያል፡፡ በዚህ ግጭት የሚሰተፉትን የሁለቱ ጎሣ ወጣቶች የታጠቁትን መሣሪያዎች ለማስፈታት በሚደረገው ጥረትም ጥቂት የማይባሉ የታጠቁ ወጣቶች ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ሸሽተው መግባታቸው ለአገራችን የፀጥታ ስጋት እንዳይሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል መንግስታት ትኩረት ማስጠታቸው ያስማሰግናቸዋል፡፡ ሌላው የደቡብ ሱዳን ወቅታዊ ችግር የተለያዩ የአስተዳደር ኃላፊዎች ሥራ በዝምድና የማስራትና በየደረጃው በሚገኙ የተለያዩ የሙስና ችግሮች ወስጥ ማዘፈቅ ነው፡፡ ይህ የነገዋ ደቡብ ሱዳን ላይ ከወዲሁ ተስፋ እንዳይኖር ከሚያደርጉ ጉዳዮች አንዱ **እንደሚሆን የአሜሪካው የውጭ ግንኙነት ም/ቤት ተመራማሪ ክርስቶፈር አሌሲ ይገልፃሉ፡፡**

የጁባ መሪዎች ከካርቱም ጋር ያላቸው አለመግባባት እስኪፈቱ ድረስ ጁባ እያመረተች ለውጭ ገበያ ታቀርበው የነበረውን የነዳጅ ምርት ማቋረጧና በዚሁ ምርት ላይ 98 በመቶ የተመሠረተው የአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ መጥፎ ድባብን ማሳደሩ አልቀረም፡፡ ጁባ በዚህ ምክንያት **ያለባት** ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋቱ **ይጠቀሳል፡፡** ሰሜኑ በበኩሉ ለኢኮኖሚው **ሁነኛ** ግብአት የነበረወና ከ75 በመቶ በላይ የኢኮኖሚው ምንጭ ተማስርቶበት የነበረው የነዳጅ **ምርት** ምንጮችን ለደቡብ ማስረከቡ ሁለቱ ወገኖች ጦርነታቸውን ረዘም ላለ ጊዜ ለመቀጠል የማይችሉ **ኢኮኖሚዎች እንዳላቸው** ያስገነዝባል፡፡

የሁለቱ ሱዳኖች ህዝቦችና **መሪዎቻቸው** ለዘመናት የቆየ የእርስ በርስ ጦርነት ወስጥ ሲዳከሩ መኖራቸው አገራቱ ወደዱም ጠሉ ጦርነት የጋራ ቋንቋቸው እንዲሆን አድርጓቸዋል፡፡ ሆኖም **ወዳጅ ጎረቤት አገሮችና** ዓለምአቀፍ ማህበረሰቡ ጠንከር ያለ ተሳትፎ ካላደረጉ ችግሩ ይበልጥ ወደአልታሰበ አቅጣጫ እንዳያመራ

ያሰጋል፡፡ እንደዓለምአቀፉ የቀወስ ቡድን ትንተና ከሆነ በተለይ የሰሜኑ ገዥ ፓርቲ ብሐራዊ ኮንግረስ ፓርቲ በወስጡ የአክራሪዎችና የጦረኞች ይበልጥ ተደማጭነት እያገኙ ከመምጣትና የውስጥ የፖለቲካ አለመረጋጋት አንፃር ፓርቲው አደጋ ላይ ከወደቀ ሰሜኑ ከደቡቡ ጋር እስከዛሬ ድረስ የመጣበትን የድርድር ርቀት ሊቀለብሰው እንደሚችል ይገለፃል፡፡

በፓርቲው ወስጥ ጥግ የሚገጡ አክራሪዎች የበላይነታቸው እየገዘፈ መምጣት እንደጀመረ የቀድሞው በዳርፉር ጉዳይ የአሜሪካን ልዩ መልዕክተኛና በጆርጅታውን ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲ ፕሮፌሰር አንድሪው ናትሲዮስ “ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንና ዳርፉር፡ ሁሉም ማወቅ የሚገባው ጉዳይ” በሚል መጽሐፋቸው ላይ ባቀረቡት ሐተታ ከዓመት በፊት የሱዳን ጎረቤት መንግስታት ከሃይማኖትና እምነት ተፅዕኖ ስር ያልነበሩ ሲሆን አሁን በግብፅ፣ በሊቢያ፣ ቱኒዚያና የመን የአልበሽር ፓርቲ ደጋፊ የሆኑ ሙስሊም ወንድማማቾች ወደ ሥልጣን እየመጡ ይገኛል፡፡ ይህን ተከትሎ በሱዳን ገዥ ፓርቲ ወስጥ የግብፅና ቱኒዚያን ህዝቦች ዓይነት ተመሳሳይ አመፅ በሱዳን ላለማየት በፓርቲው ወስጥ የዚህን ርዕዮት የሚያቀነቅኑ ባለሥልጣናት በፓርቲው ወስጥ እንዲገኑ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህን ተከትሎ አልበሽር ፓርቲያቸውን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ኃይሉ አላቸው ብሎ ለመናገር አያስደፍርም ይላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የሰሜን ወታደሮች በተቻለ አቅም ከካርቱም ርቀው በዳርፉር፣ ደቡባዊ ኮርዶፋን፣ በአቢዬ፣ የቀይ ባህር ተዋሳኝ በሆነው የቤጃና ሌሎች ያልተረጋጉ ግዛቶች እንዲወጡ በማድረግ ከአክራሪዎቹና ከወታደሩ ኃይል ሊቃጣ የሚችል ግልበጣን ለመከላከል አልበሽር የሚያደርጉት የራስ መከላከል ስትራቴጂ እንደሆነም ናትሲዮስ ይከራከራሉ፡፡

የዚሁ አካል እነደሆነ የተነገረለትንና አልበሽር በየካቲት ወር ላይ 13 ጀነራሎችን ከሥራ የማሰናበታቸውን ምክንያት ለዚሁ ማስረጃነት ያቀርባሉ፡፡ በተለይ አብዛኞቹ ወታደራዊ ኃላፊዎች ባላቸው የእምነት ጥንካሬ በሚል በቀድሞ የአገራቱ ብሐራዊ ም/ቤት አፈጉባኤና ኦሳማቢን ላደን ወደ ሱዳን እ.ኤ.አ. በ1991 እንዲመጣ ባደረጉት ሀሰን አልቱራቢ ተመርጠው የተሾሙ በመሆኑ፡፡ የዳርፉር፣ የኑባ ተራሮች፣ የሴናር፣ የብሉ ናይል፣ የቤጃና ሌሎች በካርቱም የሚገኙ ሲቪክ ተቋማት ከደቡብ ሱዳን ነፃ አወጪ ኃይል ጋር ታላቅ ትብብር በመፍጠር በሽር ከሥልጣን እንዲወርዱ እንዳያደርጉ የሚለው ፍራቻም የአልበሽር መንግስት የጦርነት ነጋሪነቱን በአቢዬና ከላይ በተጠቀሱት ግዛቶች ላይ የመነሰሙና የብሔራዊ ስሜት መቀስቀሻነት መጠቀም አንድ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

የአልበሽር መንግስት ተግዳሮቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ በመንግስቱ ወስጥ ከፍተኛ ሙስና እንደተንሰራፋና ለዚህም በዋቢነት በናታሲዮስ የቀረበው ጉዳይ አምና ካርቱም 200 ታንኮችን ገዝታ ሁሉም በብቃት ለመሥራት የቴክኒክ ችግር የነበረባቸው መሆኑና ምርመራ ሲካሄድም ችግሩ የሙስና እንደሆነ መደረሱን

ይጠቀሳል፡፡ በሌላ በኩል የአገሪቱ ኢኮኖሚ እየተዳከመ ከሜዱ ጋር ተይይዞ በአገሪቱ ወስጥ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ጣሪያ ከመንካቱ በላይ በተለያዩ የመንግስትና የፓርቲ አደረጃጀቶች እንዲገቡ የተደረጉ ከ10 ሺህ በላይ እስላሚክ የበሽር ደጋፊዎች ከሥራ እንዲሰናበቱ ለማድረግ እየታሰበ መሆኑ በራሱ ለአገር ወስጥ ፖለቲካ አለመረጋጋትን ይፈጥራል፡፡ እንደ አንድሪው ናታሲዮስ ገለጻ፡፡

## <u>አካባቢያዊና ዓለምአቀፋዊ ተፅዕኖ</u>

ደቡብ ሱዳን ነፃነቷን ካወጀች ወዲህ ኢትዮጵያወያንን ጨምሮ በርካታ የአጎራባች አገሮች ባለሀብቶችና ግለሰቦች በደቡብ ሱዳን ውስጥ በተለያዩ የሥራ መስኮች ላይ ተሠማርተዋል፡፡ ገንዘባቸውን ማፍሰስ የጀመሩ ባለሀብቶችና ተቋማትም ይገኛሉ፡፡ በዚህ ረገድ ኬንያ ከደቡብ ሱዳን ጋር ያላት ግንኙነት ስር እየሰደደ ከሜዱ አንፃር ልቧን ወደ ጁባ ማጋደል መጀመሯን በናይሮቢ የአሜሪካን ዓለምአቀፍ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ማቻርያ ሜኔ ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ረገድ ሁለቱን ሱዳኖች ቀደም ሲል በናይቫሺያ ያደራደረችው ኬንያ በቀጣይ ጠንቃቃ የዲፕሎማሲያዊ አቅጣጫ ላይ ካልተራመደች የገለልተኝነት ካርዷን ልታጣ እንደምትችል እኚሁ ምሁር ይገልጻሉ፡፡

ኢትዮጵያ በበኩሏ እስካሁን ሁለቱ ወገኖች ችግራቸወን በሠላም እንዲፈቱ ገለልተኛ አደራዳሪ በመሆን በጎ ተግባራትን ስታከናወን ቆይታለች፡፡ ይህንኑ ገለልተኛ አቋሟን አጠናክራ በመቀጠል ከሌሎች የኢጋድና የአፍሪካ ህብረት አገሮች ጋር በጋራ በመሆን ለዚሁ ዓላማ የተቻላትን ማበርከት ይጠበቅባታል፡፡ ኡጋንዳን የመሳሉ ጎረቤት አገሮችም የጦርነቱ አካል እንዳይሆኑ የማሳመን ሥራ ማስራት ያስፈልጋል፡፡

ሁለቱ ሱዳኖች ከነዳጅ ማስተላለፊያና ከትራንዚት ክፍያ፣ በካርቱም በኩል ይወረሱ የነበሩ የደቡብ ሱዳንን ነዳጅ የጫኑ መርከቦች ጉዳዮችና ሌሎች ሁለቱ ወገኖችን ሲያናቁሩ የቆዩ የህብት ክፍፍል፣ የዜግነት፣ የድንበር ማካለልና የመሳሰሉ ጉዳዮች እልባት እንዲያገኙ አገራቱ የተናጠል እርምጃ ከመውሰድ እንዲታቀቡና ወደሠላም ጠረጴዛው እንዲመለሱ በተለይ በኢትዮጵያና በኢጋድ በኩል ከፍተኛ የማደራደር ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ አንዱ ለመፈረም የተዘጋጀበትን የሠላም ሠነድ ሌላው ውድቅ እያደረገ ተቸገሩ እንጂ፡፡ ይህ ድርድር እ.ኤ.አ. ከ1990ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ ተመሳሳይ ተደራዳሪዎች በተመሳሳይ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ላለፉት በርካታ ዓመታት መደራደር በራሱ አድካሚ መሆኑ አይካድም፡፡

ከዚህ በላይ ግን ጁባን በማስተዳደር ባለው ኃይል ውስጥ እንደ ካርቱም ገዥ ፓርቲ ሁሉ ጥግ ረጋጮች (Extremists) ኃይልና ስብዕናቸው እየገዘፈ መምጣቱ፣ የደቡብ ኮርዶፋንና ብሉ ናይል አማፂ ኃይሎች የጁባ አስተዳዳሪዎች በአንድ ወቅት ከእነሱ ጋር አብረው የካርቱምን መንግስት

እንዳልወጉ ሁሉ ዛሬ ከካርቱም ጋር ስምምነት ቢፈራረሙ እንደከዷቸው መቆጠሩና ብሎም በፖለቲካ ተንታኞች እንደሚባለው የጁባ አስተዳዳሪዎች የፓርቲና የመንግስት ቢሮክራሲ ስርዓት ህግና ደንብ አለማክበር ለችግሩ መባባስ ምክንያት እንደሆነ ይገለጻል፡፡

በካርቱም ወገን ደግሞ ከደቡቡ ጋር የሚደረግና የሠላም አደራዳሪውን ሥራና ሥራውን የሚቃወሙ ኃይሎች መበራከታቸው የአልበሽር ፓርቲ የውስጥ ክፍፍል እንዳለ መጠቀሱም የዚሁ ችግር እልባት አለመገኘት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የፖለቲካ ተንታኞች ይገልጻሉ፡፡ አልበሽር ፓርቲያቸውን፣ የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል አባላትና የሳላፊ የሃይማኖት አቀንቃኝ መሪዎችን በብቃት ይቆጣጠራሉ ማለት እንደማይቻል ይገለጻል፡፡

ሁለቱ ሱዳኖች ተመልሰው ለዓመታት እንዳደረጉት ሁሉ ወደ ግጭት የሚገቡ ከሆነ ግጭቱ ከራሳቸው አልፎ አካባቢዊም ሆነ ዓለምአቀፋዊ ገፅታ እየተላበሰ መቀጠሉ አይቀርም፡፡

አገራቱ ለዓለም ገበያ የሚያቀርቡት የነዳጅ መጠን ከፍተኛ ባይሆንም በዓለም ላይ ያሉ ግጭቶችና የግጭቶች ስጋትን ተከትሎ ዋጋው ሽቅብና ቁልቁል ላይ ታች የሚለው የነዳጅ ዋጋ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡ በቅርቡ የአረብ አገራት ቀውስና የምዕራቡ ዓለም ከኢራን ጋር የያዘውን መፋጠጥ ተከትሎ የአንድ በርሜል ዋጋ መቶ የአሜሪካን ዶላር እና ከዚያ በላይ ሲዋዥቅ መክረሙ ይታወሳል፡፡ ደቡብ ሱዳን በሰሜን ሱዳን በኩል ተገቢ ያልሆነ የትራንዚት ክፍያ እየተጠየቅሁ ነው በሚል ወደ ሱዳን ወደብ የሚሄደውን የነዳጅ ምርቷን ካቋረጠች በኋላና በቅርቡም ሄግሊግን ከወረረችና ነዳጅ ማምረቻ መሠረተ ልማቶች እንዲወድሙ ከተደረገ በኋላ አጠቃላይ የሁለቱ አገሮች የነዳጅ ምርት ቁልቁል አሽቆልቁሏል፡፡ ይህ ደግሞ በህንድ ውቅያኖስና የሶማሊያ ባህር ዳርቻ አካባቢ ከተፈጠረው የባህር ላይ ዘረፋ፣ የናይጀሪያው የኒጀር ዴልታ ሁከትና ሌሎች ዓለምአቀፍ ችግሮች ጋር ተዳምሮ የነዳጁን ዋጋ እንዳይሰቅል ይፈራል ሲሉ በኒውዮርክ ተቀማጭ የሆነው የCity Futures አማካሪ ድርጅት የኃይል ባለሙያ ሚስተር ቲም ኢቫንስ ይገልጻሉ፡፡ ይህ በተራው በዓለምአቀፉ የፖለቲካ ስነምህዳር ላይ የራሱን መቀት ማሳደሩ ደግሞ አይቀርም፡፡ እዚህ ለይ አገራችን ኢትዮጵያ አብዛኛው የነዳጅ ምርቷን ከሱዳን እንደምታስገባ መረሳት የለበትም፡፡

የሱዳን ሁከት ሌላው የተፅዕኖ መዳፍ ኢኮኖሚያዊ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሱዳን ጋር በንግድ ከተሳሰሩ የጎረቤት አገሮች ጨምሮ በሁለቱ አገሮች የነዳጅ ምርት ዙሪያ ከፍተኛ መዋእለንዋይዋን ያፈሰሰችው ቻይና ላይ ቀላል የማይባል ጫና ይፈጥራል፡፡ በቅርቡ በቤጂነግ ጉብኝት ያደረጉት የደቡብ ሱዳኑ ፕሬዚዳንት

ሳልቫ ኪይር መንግስታቸው ከሰሜኑ ጋር የጀመረወን ግጭት እንዲያቆም የቻይናው አቻቸው ያሳሰቡትም ከዚሁ የመነጨእንደሆነ ማሰብ ይቻላል፡፡

ከዚህ ሌላ የሱዳኖቹ ግጭት እንደቀደመው ሁሉ በአካባቢው አገሮች ላይ ተጨማሪ የስደተኞች ጫና ማሳደሩ አይቀርም፡፡ በሄግሊግ በቅርቡ በተካሄደው ግጭት ብቻ 35 ሺህ ዜጎች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ ከግጭቱ አስቀድሞ በደቡብ ሱዳን 115 ሺህ ኢትዮጵያ ወስጥ ደግሞ ከ30 ሺህ በላይ ስደተኞች ይገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያያዞ በቀድሞ ጦርነቶች ቤተሰቦቻቸወን ያጡ ከ3,500 በላይ ወንድ የደቡብ ሱዳን ልጆች በተለምዶ የጠፉት ልጆች "Lost Boys" እንዲፈጠሩ ዳርጓል፡፡ አዲሱ የሁለቱ ሱዳኖች ግጭት ተጨማሪ "የጠፉ ልጆች" **አዲስ ትውልድ** አይፈጥር ይሆን? ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቅርቡ ከብሉ ናይል ግዛት ብቻ 33 ሺህ የሱዳን ስደተኞች በቤኒሻንጉል በአዳማዜን የስደተኞች ጣቢያ እንዲሰፍሩ ሲደረግ በተመሳሳይ ሌሎች ስደተኞች በሸርቆሌና ቶንጎ እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ስደተኞች ዓለምአቀፉን የስደተኞች ጥበቃ መርህ ባከበረ ሜኩ አካላዊና ሰብአዊ መብቶቻቸው እንዲከበር መደረጉ ኢትዮጵያን **አስመስግኗል**፡፡ ሆኖም የስደተኞቹ ብዛት የተፈጥሮ ሀብት ወድመት እንዳያስከትል ጥብቅ ክትትል ይፈልጋል፡፡

የሱዳኖቹ ጦርነት የአካባቢወን አገሮች ስቦ እንዳያስገባም ተፈርቷል፡፡ በተለይም ሰሜን ሱዳን የሎርድ ሬዚስታንስ አርሚ (LRA) የተሰኘወን የኡጋንዳ አማፂ ቡድን ትደግፋለች ስለዚህም ከደቡብ ጦር ጋር አብረን እንሰለፋለን በማለት በቅርቡ የኡጋንዳ መከላከያ ኢታማዦር ሹም ጀነራል አሮንዳ ንያካሪያማ መግለፃቸው ይህንኑ አጠናክሮታል፡፡ እንደ ጀነራሉ አባባል ደቡብ ሱዳንን ከሰሜኑ የአየር ጥቃት ለመታደግ የኡጋንዳ አየር ኃይል **ድጋፍ** የሚያደርግ እንደሚሆንና በቅርቡም አንዳንድ የደህንነት ተንታኞች እንደሚገልጹት ኡጋንዳ የገዛቻቸወን ጄት አወሮፕላኖች ለዚሁ ዓላማ ልትጠቀም ትችላለች፡፡

ኡጋንዳ በደቡብ ሱዳን **የጦርነት** አረንቋ የምትገባ ከሆነ **ደግሞ** በሶማሊያ የሠላም ማስጠበቅ ሥራ ላይ የተሠማራው የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮ አብዛኛው የኃይል ተዋፅኦ ከኡጋንዳ ከመሆኑ አንፃር ኡጋንዳ ወታደሮቿን በሶማሊያ እንዲሁም LRAን ለመውጋት በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ በኮንጎና ተጨማሪ ኃይል በደቡብ ሱዳን መመጠር አደጋው የከፋ ይሆናል፡፡

ሌላው የዚሁ ግጭት አሉታዊ ወጤት የምግብ ሸቀጦች መናራቸው ነው፡፡ በተለይ የደቡብ ሱዳን አብዛኛው የገጠር ህዝብ ቀደም ሲል በአነስተኛ እርሻና በእንስሳ ተዋፅኦ ወጤቶች ላይ የተመሠረቱ ምግቦችን ይጠቀም የነበረ **ቢሆንም ከሰሜን ሱዳን፣ ኬንያና ኡጋንዳ የሚገቡ የምግብ ሸቀጦች የአገሬውን ህዝብ የአመጋገብ ዘልማድ እንደለወጡት ይነገራል**፡፡ የምግብ ሸቀጦችን **ጨምሮ** ከግጭቱ በኋላ የሰሜን ወገን

ከካርቱም ይገቡ የነበሩ ምንም ዓይነት ሸቀጦች ወደ ደቡብ የሱዳን ክፍል እንዳይልፍ እገዳ መጣሉ ችግር አስከትሏል፡፡ የምግብ ሸቀጥ ዋጋ በእጥፍ እንዲጨምር ያደረገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ቤንዚን አምራች በነበረችው ደቡብ ሱዳን 1 ሊትር ቤንዚን እስከ 54 ብር የሚሸጥበት ሁኔታ ሜጠሩ **ጭምር በተጨማሪ** የሸቀጦች ዋጋ እንዲጨምር አድርጓል፡፡

## <u>አማራጮች</u>

የሠላም አማራጮች እንዲማጡ ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ሰፊ ሚና መጫወት ያለበት ሲሆን በተለይ አሜሪካና ቻይና የአንበሳውን ድርሻ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ሆኖም ዋናውን የሚደራደር ሚና የአፍሪካ ህብረት ሊጫወት እንደሚገባ ይታመናል፡፡ አሜሪካ ለደቡብ ሱዳን አላት ከሚባለው ያደላ ፖለቲካዊ ድጋፍ እኩል ተፅዕኖ ፈጣሪ ከ**መ**ሆን ይልቅ የአደፍራሽነት ሚናዋ **እንዳያመዝን በብዙዎች የክልሉ ተመራመሪዎች** ይፈራል፡፡ በተለይ በቅርቡ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት የቀድሞዋ የአፍሪካ ጉዳዮች ኃላፊና አሁን በአሜሪካ የውጭ ግንኙነት ም/ቤት ወስጥ የአፍሪካ ጥናት ክፍል ወስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙት ጄንዳይ ፍሬዘር በሰጡት መግለጫ ሁለቱም ሱዳኖች የችግሩ ምንጭ ናቸው ብለን ስትራቴጂክ ስህተት ሜፀም የለብንም ይልቁንም ሁለቱንም እኩል በሚዛኑ ከማስቀመጥ ይልቅ የካርቱም መንግስት ብቸኛው የችግሩ መንስኤና ወራሪ ኃይል ብለን ሜረጅ ይገባናል ሲሉ መናገራቸው የአሜሪካን ገለልተኝነት ያስጠረጥራል፡፡

ተመድ ሌላው ለሱዳን ሠላም ባለድርሻ አካል ነው፡፡ በተለይ በሱዳን ዳርፉርና አቢዬ የተሰማራው የሠላም አስከባሪ ኃይል ሠላም ከማስከበርና ሰብአዊ ድጋፎችን ከሜድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ **በዚሁ ረገድ በአቢዬ የተመድ ቆብን ተላብሶ የሠላም ማስከበር ሥራውን በአግባቡ እየተወጣ እንደሆነ የሚነገርለት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከሠላም ማስከበር ሥራዎቹ ባለፈ በህዝቡ ሰፊ ተቀባይነትን በተለይም ሲጋጩ በነበሩት የዲንቃና ሚሲርያ ጎሣዎች ዘንድ አመኔታ አግኝቶ የሚያስመሰግን የማህበራዊና ሌሎች አገልግሎቶችን በማበርከት ላይ መገኘቱ የሁሉን ኢትዮጵያዊ ልብ ያሞቀ ጉዳይ ነው፡፡**

ሁለቱ ሱዳኖች ተሜል**ሰው የጦርነት ነጋሪት መጎሰማቸውን** የጠሉትን ያህል የወደደቱም አልጠፉም፡፡ ጄን**ዳ**ይ ፍሬዘርን ጨምሮ አንዳንዶች የሁለቱ ሱዳኖች መንግስታት በድርድር ለመፍታት ያልቻሉትን ግትርተኝነት በጠንቻ የመሞካከር ዕድል የድርድሩ አንድ አካል አድርገው ወስደዋል፡፡ በወታደራዊ ሜዳ የተገኙ አንዳንድ

ወጤቶችን በጠረጴዛ ለማስቀመጥ ወይም የድርድሩን አቅጣጫ ለማምራት የራሱ ጠቀሜታ እንደሚኖረው እነዚህ አካላት ያምናሉ፡፡ ችግሩ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ወደሆነ ጦርነት ያመራ እንደሆነ ግን **የማይመልሱት እሳት ይሆናል**፡፡

ደቡብ ሱዳን ከ**ካርቱም** ጋር በነዳጅ ማስተላለፍና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ተግባራዊ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ የኢኮኖሚ ትስስሩን ከሰሜኑ ይልቅ ወደ ምሥራቅና ወደ ደቡብ የአገሪቱ አጎራባች አገሮች **በማተኮር** ከሰሜን ሱዳን ጋር ያለውን ጊዜያዊ ችግር ሊፈታ እንደሚችል **የጁባ አስተዳደርና አንዳንድ ተንታኞች እንደአማራጭ ያስቀምጡታል፡፡ ነገር ግን በቅርቡ ኢጋድ የክልሉን ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ትብብርና ዘለቄታዊ ጥቅም ከማሳደግ አንፃር ያስቀመጠውን የውህደት ዕቅድ** (Minimum Integration Plan) **ወደ ጎን እንደማድረግ ሊታይ ይችላል**፡፡

ሆኖም በተለይ አሜሪካ፣ ሩሲያና ቻይናን የመሳሰሉ የተመድ የፀጥታው ም/ቤት **አባል** አገራት ጨምሮ ሌሎችም ለሁለቱ ሱዳኖች ከየአገራቸው ጥቅም አንፃር የሚያራምዱት አቋም የሱዳኖቹ የፖለቲካ ድርድር ከተመድ ይልቅ በአፍሪካ ህብረት ቢያዘ የተሻለ እንደሆነ ተንታኞች ይናገራሉ፡፡ **ከዚያ ይልቅ** ተመድ ወደሁለቱ አገሮች የሚገቡ የጦር መሣሪያዎች ላይ ቁጥጥር ቢያደርግ ተመራጭ እንደሚሆን ይነገራል፡፡ ቻይና ለሰሜን ሱዳን አየር ኃይል በርካታ መሣሪያዎችን እንዲሁም ሩሲያ አንቶኖቭ አወሮፕላኖችንና Sukhoi Su-25 የተሰኙ ጄቶችን የሸጡ ሲሆን አሜሪካ በድርሻዋ ለደቡብ ሱዳን በዓመት ከመቶ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ የሚገመት የጦር መሣሪያ ድጋፍ እያደረገች **እንደምትገኝ** መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በቅርቡ በተመድ የፀጥታው ም/ቤት ሁለቱ ሱዳኖች የያዙትን የፀብ አጫሪነት ባህሪ የሚያስተካክሉ ከሆነ ማዕቀብ እንዲጣልባቸው የሚጠይቅ ሰነድ በአሜሪካ አዘጋጅነት መቅረቡ ይታወሳል፡፡ ይህ ውሳኔ በአፍሪካ ህብረት የቀረበውን ተመሳሳይ አቋም የሚደግፍ እንደሆነና ወጤት የሚያስገኝ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ተመድ ይህን መሰል ማዕቀብ የሚያሳልፍ ከሆነ በሁለቱም ወገኖች ላይ ያልተበላለጠ ውሳኔ መሆኑንና እኩል ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኑን ብሎም ከሠላም ፈጣሪነቱ አልፎ የጀርባ አጀንዳዎችን ማስፈፀሚያ **እንዳይሆን** ማረጋገጥ ተገቢ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በቅርቡም ከ150 በላይ የአፍሪካና አረብ አገሮች ሲቪክ ተቋማት በጋራ ለተመድ **ባስገቡት ደብዳቤ** የጠየቁት ይህንኑ ነውና፡፡

ሌላውና ዋነኛው የሠላም አማራጭ ሁለቱ ኃይሎች የሚክዱትን ነገር ግን መረጃዎች በግልፅ የሚያመላክቱትን በኮርዶፋንና በብሉ ናይል ግዛቶች እንዲሁም በዳርፉርና ሌሎች ግዛቶች ወስጥ በሚደረጉ ግጭቶች ወስጥ አንዱ የሌላውን ኃይል ለማዳከም የሚያደርጓቸውን የእጅ አዙር ጦርነቶች (Proxy War) ማቆም ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚያ ባለፈም የካርቱም መንግስት በእነዚህ አካባቢዎች ለህዝቡ ሰብአዊ እርዳታ እንዳይደርስ ያደረገውን

ማዕቀብ ማንሳት ይኖርበታል፡፡ **በተጨማሪም** በኑባ ተራሮች፣ በአልቡራም፣ በኡምዱርየንና ሄይባን ክልሎች ወስጥ የሚደረገወን የሚያቋርጥ የቦንብ ድብደባ ማቆም ይገባዋል፡፡

የአፍሪካ ህብረት መፍትሄ ለሚፈላለግ ባለ 7 ነጥብ የሠላም አማራጭ አዘጋጅቶ ያቀረበ ሲሆን እስከአሁን ሁለቱም ወገኖች ይህን ሀሳብ ተቀብለዋል፡፡ **ካርቱም** በመርህ ደረጃ፡፡ ይህ ሀሳብ ሁለቱ ወገኖች ግጭታቸወን በአፋጣኝ እንዲያቆሙ፣ ወታደሮቻቸወን ከግጭት ቦታዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያወጡ፣አንዱ የሌላወን አሚፂ እንዳይደግፍና ፀብ የሚጭሩ ፕሮፓጋንዳዎችን ማጠቀም እንዲያቆሙ ይጠይቃል፡፡ ሆኖም እስካሁን ድረስ ሁለቱም ወገኖች **መቆራቆሱን** ያላቆሙ መሆኑ **በሠላም አማራጩ** ተፈፃሚነት ላይ ብዙዎች ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ከዚያም አልፎ አገራቱን አስከዛሬ ለሚደርደር እጅግ አበረታች እንቅስቃሴ ሲያደርግ የቆየወና በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ **ፕሬዚዳንት** ታቦ ሞቤኪ የሚመራው የአፍሪካ ህብረት ከፍተኛ አስፈፃሚ ፓናል (AUHLIP) ላይ በደቡብ ሱዳን በኩል በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች **የፓናሉን** ቀጣይነትና ተደማጭነት ላይም አሉታዊ ጥላ እንዲያጠላበት አድርጓል፡፡ በዚህ ረገድ አፍሪካ ህብረት ከኢጋድ ጋር ብዙ ሥራዎች እንደሚጠብቁት አመላካች ነው፡፡

**ቀደም ሲል በ2005ቱ በአጠቃላይ የሠላም ስምምነቱ ውሳኔ ያልተሰጠባቸውና አሁን የግጭቱ መንስኤ እየሆኑ ያሉ ክልሎች ጉዳይ በስምምነቱ ወደፊት በህዝባዊ ምክክር ጉዳያቸው እንደሚፈታ ያስቀምጣል፡፡ ሆኖም ይህ ምክክር የሚባለው ሰፊ ጉዳይ በምን መልኩ አቅጣጫ ሊቀመጥለትና ሊተገበር እንደሚገባ ከውሳኔ መድረሱ የሁለቱ ሱዳኖችና የአደራዳሪዎቻቸውን ጥበብና ብስለት ይጠይቃል፡፡**

**በተለይ ኢትዮጵያ ከሱዳን በቅርብ ርቀት እየገነባች ያለችው ለብዙዎቻችን የነገዋ ኢትዮጵያ ተስፋ የሆነው የህዳሴው ግድብ፣ የአሸባሪነት አደጋ፣ ከሻዕቢያና መሰል የጥፋት ኃይሎች በኩል ሊነሱ ከሚችሉ የፀጥታና የአለመረጋጋት አደጋዎች እንዲሁም ከሁለቱ ሱዳኖችና በክልሉ በአጠቃላይ እየገነባች ካለችው አጠቃላይ የኢኮኖሚያዊና የመሠረተ ልማት ትስስር አኳያ ኢትዮጵያ ለሱዳኖቹ ችግር እልባት የማግኘቱን ሥራ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበርና በፋና ወጊነት ልትመራው ይገባል፡፡ ይህንኑ በማየት ላይ መሆናችን ደግሞ ኢትዮጵያን ያስመሰግናታል፣ በሁለቱ አገራት ህዝቦችና መንግስት በኩል የሚኖራት ተቀባይነትንም የላቀ ያደርገዋል፡፡ ይህ ተጠናክሮ ይቀጥል እንላለን፡፡ ሠላም፡፡**

***ፀሐፊውን በሚከተለው የኢሜይል አድራሻ ማግኘት ይቻላል*** J ***n_tedla@yahoo.com***